በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ከእነዚህ ደግሞ ራቁ


መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com


*<u>ቦታ፦</u>* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**የካቲት ፲፯ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>ከእነዚህ ደግሞ ራቁ</u>

- “ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ።” ***<u>ካልዕ ጢሞ 3፡1-5፡፡</u>***
- **ይህ መልዕክት በተጻፈበት ዘመን ቅዱስ ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሆኖ የመጨረሻ ፍርዱን ይጠባበቅ ነበር፡፡ ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስ ግን በኤፌሶን ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡**
- **ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስን በዘመኑ እንዲሁም በኂለኛው ዘመን ስለ ሚነሱ ሐሰተኞች መምህራንና ሐሰተኞች ክርስቲያኖች ጽፎላቸዋል፡፡**
- **ቅዱስ ጳውሎስ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ እምነት ያጡ ስለመሆናቸው አስጠንቅቆ ጽፎለታል፡፡ እንደዚህ ካሉ ሰዎችም እንዲርቅ መክሮታል፡፡**
- **ቅዱስ ጳውሎስ በመጨረሻው ቀን ሊመጣ ይችላል፣ ይመጣ ይሆናል፣ ላይመጣ ይችላል፣ … እያለ በጥርጣሬ ሳይሆን በማስረገጥ ‹‹ለማስረዳት የሚያስቸግር የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ እወቅ›› ያለው መሆኑን እንረዳ፡፡**
- **ወገኖች ይህ አሁን ያለንበት ዘመን የሚያስጨንቅ ነገር የበዛበት ዘመን አይደለምን? ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ መልዕክቱ ቀዳ ጢሞ 4፡1 ላይ** ‹‹መንፈስ ግን በግልጥ። በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው ሃይማኖትን ይክዳሉ ፡፡ » በማለት ጽፎልናል፡፡
- **ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው በሁለተኛ መልዕክቱ ደግሞ ከቤተክርስቲያን ውጪ ሳይሆን እርሱ በሚኖርበትም ዘመን ሆነ ከዚያ በኂላ በቤተክርስቲያንም ስለሚገጥሙት የሰዎች ዓይነትና ከነርሱም እንዲርቅ ጽፎለታል፡፡**

# ከእነዚህ ደግሞ ራቁ

- አሁን የምንኖርበት ዓለም ብዙዎች ከእግዚአብሔር እውነት ራሳቸውን ያራቁበት ከእግዚአብሔርም ጋራ ያላቸውን ግኑኙነት እያቋረጡ የሚገኙበት ነው፡፡
- ቀዳ ጢሞቴዎስ ምእራፍ 4 እና ካልዕ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ሁለቱም የሚናገሩት ስለምንኖርበት ዘመን ሲሆን ካልዕ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ግን የበለጠ ተተንትኖ የተቀመጠ ነው፡፡
- በምንኖርበት ዘመን ማኅበረሰባችን በቴክኖሎጂ፣ በዕውቀትና በሌሎችም ዕድገት እያሳየ ከመሆኑ ጎን ወንጌልም ለዓለም እየተሰበከ ቢሆንም ብዙዎች ደግሞ ከእውነተኛይቱ ሃይማኖት እየወጡ ነው፡፡
- መንፈስቅዱስ ስለምንኖርበት ዘመን አስጨናቂነት ነግሮናል፡፡
- አሁን የምንኖርበት ዓለም ያለንበትን ሐዘን እፎይ ሳንል ቀጥሎ የሚሆነው አሳዛኝ ታሪክ የሚተካበት ነው፡፡ ዛሬ የምንናገረው ስለ ነዳጅ ዋጋ፣ ስለ ጦርነት፣ ስለ ሱናሚ፣ ስለ መሬት መናወጥ፣ በቤታችን ስላለው ችግር፣ ስለ አደንዛዥ እጽ፣ … አይደለም፡፡
- አንዱን አስከፊ ነገር ሳንወጣው ሌላው መተካቱ ግን ዘመኑን አስጨናቂ ያደርገዋል፡፡
- በምንኖርበት ዘመን ያሉትንና ወደፊት የሚኖሩ ሰዎችን ጠባይ እስኪ በጥቂቱ እንመልከት፡፡ ዘመኖቹንና ሰዎቹን ‹‹የመጨረሻ ዘመን›› ብሎ የጠራቸው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡
- በመንፈስቅዱስ ረዳትነት አሥራ ስድስት ዓይነት ሰዎችን ወይም የሰዎችን የመጨረሻ ዘመን ጠባያት እንመለከታለን፡፡
- እነዚህ ዓይነት ሰዎች በጢሞቴዎስ ዘመን ነበሩ እንዲሁ ዛሬም ይኖራሉ፡፡

1. *ራሳቸውን የሚወዱ፡-* በራሳቸው ታናሽ ዓለም ብቻ የሚሆነውን የሚያስቡ ናቸው፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች በራሳቸው ዓይን መልካም የሆነውን ብቻ ይሠራሉ፣ ይናገራሉ፡፡ ጌታችን ግን ያለን ‹‹ በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።» ነው፡፡ ***ማር 8፡34፡፡***

# ከእነዚህ ደግሞ ራቁ

2. *ገንዘብን የሚወዱ፡-* የብልጽግና ወንጌል ስብከት ዛሬ በዓለም እየተስፋፋ ነው፡፡ ሰዎች ለገንዘብ ሲሉ የጋዛ ቤተሰቦቻቸውን ይገድላሉ፡፡ ገንዘብን ማግኘት ኃጢአት አይደለም፡፡ ኃጢአቱ ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር በላይ ገንዘብን መውደዳችን ላይ ነው፡፡
3. *ትምክህተኞች፡-* ትምክህተኛ ሰው የራሱን ሥራ በተሻለ መንገድ እንዲሠራ የሚነግረውን ወይም የሚመክረውን ማንንም አይፈልግም፡፡ ራሳቸው የሠሩትን ሥራና ችሎታቸውን አጋንነው፣ ለማኅበረሰቡም ስላላቸው ጥቅም ራሳቸውን ምሳሌ አስመስለው ያቀርባሉ፡፡
4. *ትዕቢተኞች፡-* እነዚህም ትዕቢት በውስጣቸው አለባቸው፡፡ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ያውቃል፡፡ የትዕቢት መኖሪያው ልብ ነው፡፡ ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር እርሱ መርምሮ ያውቃል፡፡
5. *ተሳዳቢዎች፡-* እንዲህ ያሉት እግዚአብሔር አብን፣ እግዚአብሔር ወልድን፣ እግዚአብሔር መንፈስቅዱስን ከመሳደብ እንኳ አይመለሱም፡፡ ምሕረትን እንዳያደርግላቸውም ይዘብቱበታል፡፡ *መዝ 88፡1-52፣ ቀዳ ቆሮ 4፡12፡፡*
6. *ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፡-* ዛሬ ያሉትን አንዳንዶች ወጣቶችን ተመልከቱ፡፡
7. *የማያመሰግኑ፡-* እግዚአብሔር ላደረገላቸው ሁሉ አያመሰግኑም፡፡ ለእግዚአብሔር ስላደረገላቸው ምስጋና የማያቀርቡ ከሆኑ ለሚመስሏቸው የሰው ወገኖችም ስለተደረገላቸው መልካም ነገር ማመስገን ይሳናቸዋል፡፡
8. *ቅድስና የሌላቸው፡-* ኃጢአተኞች ሆነው ለተቀደሰ ነገር ንቀት ያላቸው ይሆናሉ፡፡
9. *ፍቅር የሌላቸው፡-* የፍቅር ልብ የሌላቸው ልበ - ቀዝቃዞች ናቸው፡፡ ጌታችን እንዲህ ያሉትን እፉኝት ብሎአቸዋል፡፡ ማቴ 12፡34፡፡
10. *ዕርቅን የማይሰሙ፡-* ለጠብ ለክርክር፣ ለልዩነት፣ ወዘተ ብቻ አድልዎ የሚያደርጉ፡፡ *ቀዳ ሳሙ 7፡14፡፡*

# ከእነዚህ ደግሞ ራቁ

11. *ሐሜተኞች፡-* እንዲህ ያሉ ሰዎች በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን የበዙ ናቸው፡፡ አንዳንዶች የወንድሞቻቸውን ወይም የእህቶቻቸውን ስም እጅግ በሚያስከፋ ሁኔታ በየሥፍራው ያነሳሉ፡፡ ይህንም የሚያደርጉት በቤተ ክርስቲያን ዙሪያም ሆነ ከዚያ ውጪ የተሻለ ስም ለማግኘት፣ ራሳቸውንም እናደርሰዋለን ብለው ያሰቡበት ሥጋዊ ቦታ ለማድረስ ካላቸው የተናቀ የሥጋ ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡ ይህንም የሐሜት ጥማቸውን ለማርካት ዓለም ለፕሮፖጋንዳ የምትጠቀምበትን የመገናኛ ዘዴ፣ የኢንተርኔት ብሎጎችን፣ ካገኙ ሌላም ዘዴዎችን ነገ የሚገለጥባቸውን የእውነት ብርሃን ሳያስቡም ቢሆን በጭፍን ይጠቀማሉ፡፡ ‹‹ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።» *2ኛ ተሰ 2፡11፡፡* «ሐሰትን የሚናገር አፍ ይዘጋል።» *መዝ 62፡11፡፡*
12. *ራሳቸውን የማይገዙ፡-* ዛሬ ዛሬ ይህ የብዙዎች መላያ ጠባይ ነው፡፡ ዝሙት፣ ግብረ ሰዶማዊነት… ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሳይቀር…
13. *ጨካኞች፡-* ሰዎች ዛሬ በመንፈስቅዱስ ፈንታ በደመ ነፍስ የሚነዱ ርኅራኄ የጎደላቸው እንስሳት እየሆኑ ነው፡፡
14. *መልካም የሆነውን የማይወዱ፡-* በዚህ ዘመን መልካም መሆ፣ በጎ ማድረግ፣ የእግዚአብሔር ሰውም መሆን በብዙዎች ዘንድ የመጠላት ምንጭ ነው፡፡ *ዮሐ 15፡18፣ ቀዳ ዮሐ 3፡13፡፡*
15. *ከዳተኞች፡-* ሰዎች ቃላቸውን መጠበቅ ተስኖአቸው ከዳተኞች ሆነዋል፡፡ አንዳንድ ሰዎችም ራሳቸውን የሚመለከቱበት መነጽር እያጡ ነው፡፡
16. *ቅንጦትና … ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፡-* አንዳንዶች በቤተ ክርስቲያን ሥጋቸውን የሚያስደስትን ነገር ይመርጣሉ የሚል ነው፡፡ ከመንፈሳዊ ሕይወት ይልቅ በማኅበራዊ ሕይወት፣ በግርግሩ ላይ ያተኩራሉ፡፡

- ከላይ የተገለጡት ጠባያት ያላቸው እነዚህ የአምልኮት መልክ ያላቸው ኃይሉን ግን የካዱ አማንያን ናቸው፡፡
- እነዚህ ሰዎች ሕይወታቸውን መንፈስቅዱስ ይመራ ዘንድ ያልፈቀዱ ናቸው፡፡
- አስመሳይነት እያደገ ነው፡፡ ወደፊትም እያደገ ይቀጥላል፡፡
- እነዚህ በመልዕክቱ የተጠቀሱት ሰዎች ከገቡበት የኃጢአት ኑሮ ነጻ የሚያወጣቸውን የእግዚአብሔርን ኃይል አይሹትም፡፡

# ከእነዚህ ደግሞ ራቁ

- ከእግዚአብሔር ጋር የሆነ እውነተኛ ግኑኙነት የዕውቀት ወይም የሞያ (ፕሮፌሽን) ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁኑ በእግዚአብሔር ፊት የተወደደውን በጎ ሕይወት ከሃይማኖት ጋር ይዞ መገኘት እንጂ፡፡
- እግዚአብሔርን በማገልገል ሕይወት መጽናት፣ የመንፈስቅዱስንም ፍሬ ማፍራት እርስ በርስ መዋደድ፣ ጌታችን በዕለት ዓርብ በከፈለልን መሥዋዕትነት ባወረሰን ርስቱ፣ ባጎናጸፈን ውስጣዊ ሰላም፣ ደስ በመሠኘት ይህን የሚያስጨንቅ ዘመን ማለፍ ያስፈልጋል፡፡
- ሁላችንም ትዕግስት ያስፈልገናል፡፡ የሚያስፈልገንም ትዕግሥት ከላይ በተጠቀሱት ድክመቶች የተወሰደውን የሰው ወገን ለማገልገል የሚያስችለን ትዕግሥት ነው፡፡
- ለእኛ ሊያደርጉልን የምንፈልገውን ያህል ለሌሎችም ያንኑ ማድረግ የምንችልበት ደግነትና ርኅራኄም ሊገኝብን ያስፈልገናል፡፡
- በመጨረሻው ቀን የክብርን አክሊል እንዲያቀዳጀን በዚህ አስጨናቂ ዘመን በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነታችንን አጽንተን ለርሱ ታማኝነታችንን ማሳየት ይገባናል፡፡
- ጌታችን ‹‹ማለዳም። ሰማዩ ደምኖ ቀልቶአልና ዛሬ ይዘንባል ትላላችሁ። የሰማዩን ፊትማ መለየት ታውቃላችሁ፥ የዘመኑንስ ምልክት መለየት አትችሉምን?» *ማቴ 16፡3፡፡*
- ቅዱስ ጳውሎስም «ወደ እስያ ከገባሁበት ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ፥ በትሕትና ሁሉና በእንባ ከአይሁድም ሴራ በደረሰብኝ ፈተና ለጌታ እየተገዛሁ ዘመኑን ሁሉ ከእናንተ ጋር እንዴት እንደ ኖርሁ እናንተው ታውቃላችሁ፡፡» *የሐ ሥራ 20፡18-19*፡፡ እና «ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።» *ኤፌ 5፡16፡፡* በማለት ያስተማሩንን እያስታወስን መጽናትና ልንርቀውም ከሚገባን መራቅ ያስፈልገናል፡፡

# ከእነዚህ ደግሞ ራቁ

- ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ አንጻር ዓለምን ስንመለከት ዓለም ከስድስት ቢሊዮን በላይ የሆኑ ሕዝቦች መኖሪያ ብትሆንም ነዋሪዎቹ ሰዎች ግን ሁለት ዓይነት እንደሆኑ እንረዳለን፡፡

- **እነዚህም ሁለት ዓይነት ሰዎች ለእግዚአብሔር የሆኑትና ያልሆኑት ናቸው፡፡**
- ‹‹ የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም፤ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም።» ***ቆዳ ቆሮ 10፡21፡፡***
- **ይህ ዓለም ክርስቲያን እንደሆኑ በሚያስቡና አፋቸውንም ሞልተው የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንደሆኑ በሚናገሩና በእውነት ግን ከእግዚአብሔር በራቁ በርካታ ሰዎች የተሞላ ነው፡፡**
- **ይህን የምንልበት ምክንያት መልካምና ውብ የሚመስሉ በርካታ ነገሮች በእግዚአብሔር ቃል ሲፈተሹ ሰውን ከእግዚአብሔር ለመለየት የተዘጋጁ ሆነው እያገኘናቸው ስለሆነ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ከነዚህ ራሳችንን እንድናርቅ መክሮናል፡፡**
- **ከቅዱስ ጳውሎስ አስቀድሞም ጌታችን** “ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስቱ ዘንድ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ። እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ፥ አስቀድሜ ሁሉን ነገርኋችሁ።” *ማር 13፡22-23፡፡* “ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።” *ዮሐ 5፡22-23፡፡* **ብሎ በማስጠንቀቅና በማሳመን ድካሙ በተገኘባቸውም እኛ እንዳንፈርድ ብንፈርድባቸውም በድንጋጤ ግራ ተጋብተው ራሳቸውን ሃይማኖት በሚመስል ቡድን ውስጥ ከተው ሊያጠፉ እንደሚችሉ በሚያሳስብ መልኩ እንዲህ ባሉት ፈራጁ እርሱ እንደሆነ አስተምሮናል፡፡**

# ከእነዚህ ደግሞ ራቁ

- **በአገልግሎታችን ሰዎችን ስናገኝ የመጀመሪያ መልእክታችን ‹‹ሲኦል ትወርዳለህ ወይም ትገባታለህ፡፡›› የሚል በጥንቱ ወታደራዊ ሥልጠና አስተሳሰብ ላይ ብቻ የታነጸ ማስፈሪያ መሆን የለበትም፡፡ በዚህ ጉዳይ እንዲህ ላሉ ለጠፉ ነፍሳት የእኛ ኃላፊነት የእግዚአብሔርን እውነት መናገርና ማስተማር ነው፡፡**
- **በድካሙ የሚገኙትንም ለመለየት ለዓለም ማድመቂያነት ከተሠሩ ነገሮች በአጋጣሚ የምንሰማውንና የምናየውን ሁሉ ከእግዚአብሔር እውነትና ነገንም እርሱ አምሽቶ በሚያነጋባት ዓለም ውስጥ ከሚሠራው ሥራው በላይ አምኖ ተገዢ መሆን ከክርስቲያኖች አይጠበቅም፡፡** ‹‹ ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ።*›› ዮሐ 7፡24፡፡* የተባልነው ለዚሁ ነው፡፡
- **ዛሬ ሰዎች መጥፎም ይሁን ጥሩ የሚፈርዱት ባሸነፋቸው ገጽታ ላይ ተመርኩዘው ነው፡፡ ይህም በሌሎች ላይ ያለንን አመለካከትና ጠባይ የሚቀርጽ ተጽእኖም የሚያሳድር አካሄድ ነው፡፡**
- **ጌታችን** ‹‹ እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል። በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፥ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም?›› **ብሎ ካስተማረን በኂላ በጎንና መልካምን እንዴት መለየት እንዳለብን ደግሞ** ‹‹ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም። መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።›› **ብሎ አስተምሮናል፡፡** ***ማቴ 7፡16-20፡፡***

# ከእነዚህ ደግሞ ራቁ

- ያልሆኑትን አስመስለው የሚቀርቡትን - የአምልኮት መልክ ይዘው የሃይማኖት ልብስ ለብሰው ኃይሉን የካዱትን - አስገራሚና ተደማጭ ቃላቶችን የሚናገሩ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሳይሆን መንግሥቱን በመቃወም የሚሠሩትን ሰዎች በተመለከተም ጌታችን ‹‹ የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።›› *ማቴ 7፡15* ብሎናል፡፡ እንዲህ ያሉት እንዳያታልሉንም አንዱና ብቸኛው መንገድ ፍሬያቸውን መመርመር ብቻ ነው፡፡
- የተፈጠረብን የቀድሞው ወይም የመጀመሪያው ተጽዕኖ መልካምም ይሁን መጥፎ የቡድኖቹ ወይም የአንዱ ሰው ቀረቤታ መልካምም ይሁን ሌላ እንደ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሚሠራውን እየጠበቅን፣ ፍሬን እየመረመርን፣ ከሚያሳስትም የቡድን ስሜት ጸድተን እውነትን እየተደገፍን መራመድ ያስፈልገናል፡፡
- ክርስቲያኖች የተጠራንለት ዓላማ እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ እጅግ የጎዱንንም ሳይቀር ይቅር ማለት ነው፡፡ ‹‹ ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።›› *ማቴ 22:37-40::* እንደተባልነው በድካማቸው ላጎደሉብን ሳናጎድል መኖር ለክርስቲያኖች የሚገባ ነው፡፡
- እንግዲህ በመጻሕፍት እንደገለጹልን በጎውንና ክፍውን ለይተን በማወቅ በማስመሰል ከምንመራው ሕይወት መለየትና ልንርቀውም ከሚገባን መራቅ ይኖርብናል፡፡ ለዚህም ከክፉው ሁሉ በመራቅ፣ ለደከሙት መቅረብ በጎ ምሳሌ ሆነን ንጽሕት ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖታችንን ጠብቀን በአምላካችን ፊት የተወደደ የሚሆንልን መልካም መዓዛ ያለው ምግባር ይዘን በፍርድ ቀን በቀኝ ለመቆም ያበቃን ዘንድ የእግዚአብሔር ቸርነት የቅዱሳን አማላጅነት አይለየን፡፡ አሜን፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።